ደራሲና ሀያሲ አለማየሁ ገላጋይ



የፍትሕ ተጋባዥ ፀሐፊ

…ጀንበር ጠልቃለች ፡፡ ከተፈጥሯዊዋ ጀንበር ጋር ሰው ሰራሿም ብርሃን አብራ ኮብልላለች ፡፡ ለባለ-ግርማው ጨለማ፣ ለዳፍንቱ እጅ ሰጥተናል፡፡ በተለይ ቤቱ እንደጭራቅ አፍ ተበልቅጦ እንዲያ ወደጥጉ አካባቢ የሚያንሸራትት የእንጦሮጦስ ጉሮሮ አብጅቷል፡፡ ከጓደኞቼ ጋር ተጠራርተን ቤቱን ሸሸነው፡፡ የብርሃን ጌታ ቀን ሲከምረው ከሞላው የብርሃን ነዶ ውስጥ አንዷ በቃርሚያነት ተበትና እንዲሁ እንደ ዶሮ እርሷን ለመልቀም…

… እውነትም ሰማዩ እንደቤቱ ውስጥ ጣሪያ ንፉግ አልነበረም፡፡ ቀን ሲያገነፍል የነበረውን ብርሃን ቢያሟጥጥም፣ እጣቢውን አልነፈገንም፡፡ ወሬ ጀመርን፤ እጅ ብቻ አይደለም አፍን የሚያጣው፤ አፍም ጆሮን አይስተውም፡፡

ከጥቂት መጨዋወቶች በኋላ ሁላችንንም ፀጥ ያሰኘ ነገር ተከሰተ፡፡ በግምት ከሃያ እስከ ሰላሳ የሚሆኑ የመከላከያ ሰራዊት አባላት (ወታደሮች) በጦር ቀጠና ስልት ተሰልፈው ከወደ እሪ በከንቱ መጡ፡፡ ቀርበውን ስናያቸው በወታደራዊ ጦር ዕቃ የተደራጁ ናቸው፡፡ ከጠበንጃም ባሻገር መጠባበቂያ የጥይት ካርታ በወገባቸው ላይ ታጥቀዋል፡፡ ሁላችንንም ያስገረመን ይሄ አይደለም፡፡ ከወታደሮቹ መካከል አካፋ፣ ዶማና ከረጃጅም አጠና የተሰራ ቃሬዛ የያዙም ነበሩ፡፡ ይሄንን የምነግርህ ዛላንበሳ ሆኜ ከመሰለህ ተሳስተሃል፡፡ መሃል አዲስ አበባ እንጂ፡፡ ጊዜውም የሩቅ እንዳይመስልህ ባለፈው ሳምንት እንጂ፡፡

አዲስ አበባ ጦር ሜዳ ናት? ጦር ሜዳ ብትሆንስ፤ የአምቡላንስ አገልግሎት አልተቋረጠ ቁስለኛ ማግለያ ቃሬዛው ምን ይሉት ጌጥ ነው? ደግሞስ የአካፋና ዶማው ጋጋታ ምንድነው? የሞተውን (የተሰዋውን) ያገኙበት ቆፍርው ሊቀብሩ? ባለፈው መንገድ ዳር ተቆፍሮ ያየሁት የእንሱ ነው የቴሌ? ምንስ ተቀበረበት? ኬብል ወይስ ሽምቅ ተዋጊ?

በእርግጥ ወታደሮቹ ዞርም ብለው አላዩንም፡፡ አልነኩንምም፡፡ ነገር ግን አለመንካት ይሄ ነው? በገዛ ፍርሃታችንም ቢሆን አፍንጫችን ላይ የነበረችው ዝንብ በርራለች፡፡ የወታደሮቹ ተልዕኮም ይሄው ነው፡፡ በገዛ ፍርሃትህ የተረጋጋች ዝንብህን እንድታባርር ማስገደድ፡፡ ወሬህን ያቆምክበት እንዲጠፋህ ማደናበር፡፡ የአምቡላንስ መጮህ፣ የአባ-ዲና መንጋጋት፣ የማዘጋጃ ቤት ስርዓተ-ቀብር… ከመቅፅበት የሚለወጡ የከተማ ቅዠቶች መሆናቸውን እንድታስብ ማስገደድ፡፡ አዲስ አበባ ብትሆንም አንድ ቀን ወታደራዊ ቃሬዛ፣ ዶማና አካፋ ስራ ላይ ሊውሉ እንደሚችሉ ማስገንዘብ… እናም የራስህን የፍርሃት አጥር ማጠባበቅ እንድትጀምር በስነ-ልቡና መውረር፡፡

ሰው ሰራሽ ስጋት ይሉሃል ይሄ ነው፡፡ ከመሬት መንቀጥቀጥ፣ ከሱናሚ፣ ከእሳተ ገሞራ፣ ከውሃ መጥለቅለቅ፣ ከመሬት መንሸራተት፣ ከመብረቅ መውረድ፣ ከከባድ ዝናብ… የላቀው ሰው ሰራሽ ስጋት፡፡

ለነገሩ ስጋት ነክሰን፣ ስጋት ተንተርሰን መኖር ከጀመርን ቆየን፡፡ የኑሮ ማሻቀብ ስጋት፣ ከአካባቢ የመፈናቀል ስጋት፣ የአሸባሪነት ስጋት፣ የብሔር ግጭት ስጋት፣ የሃይማኖት ግጭት ስጋት፣ የንግድ ዋስትና ስጋት፣ የመናገር ስጋት፣ የመዋጮ ስጋት፣ የምርጫ ስጋት፣ የስራ ዋስትና ስጋት፣ የጡረታ ስጋት፣ የመሬት ይዞት ስጋት… ስጋት ልብሱ፤ ስጋት ጉርሱ ሆነናል፡፡

እኛ ተገዢዎቹ ብቻ አይደለንም የስጋት ቁራኛ የሆንነው፡፡ ገዢዎቹም የራሳቸው ስጋት እንዳለባቸው አይጠረጠርም፡፡ የስጋቶች ናዳ ተጭነውት የተቀበረው ተገዢ ድንገት እንደ አልአዛር መቃብሩን ፈነቃቅሎ ቢነሳስ? ትልቅ ስጋት ነው፡፡ ስለዚህ ከስጋታቸው ጥንካሬ የስጋቶች ሁሉ ስጋት የሆነውን የህይወት ዋስትና ማጣት ስጋት ይጭርብሃል፡፡ እዚህ ላይ የበዕውቀቱ ስዩምን ግጥም አንዴ እንድወጣው ይፈቀድልኝ፡፡

# ፍኖተ-አርነት..2 )

ክቡር መንፈሴ ሆይ..

አንተው ህግ አርቃቂ

አንተው ፍርድ አፅዳቂ

የወህኒው ባለቤት

የወህኒው ጠባቂ

ደካማው ሰለባህ

በሀይልህ ስር ታስሮ

ያመልጥ ይሆን ሰብሮ?

ይበቀለኝ ዞሮ

ምን ያስብ ምን ያቅድ?

ምን ይከብ ምን ይንድ?

ብለህ በማውጠንጠን እረፍት ከምታጣ

ምርኮኛህን ፈትህ አንተው ነፃ ውጣ

ተገዢ ነብር፣ ገዢ ድንገተኛ አዳኝ ሆኖ እጅ ተጭራ ተቋልፏልና የሚላቀቅ አይመስልም፡፡ ስጋት ያጓትተዋል፡፡ ስጋት ገዢዎችን ሲጠናወት የቅርብ ቢሆንም ለተገዢዎች ግን አባት-አደር ውርስ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አንድ የጥንት ባላገር ለባለጊዜው እንዲህ ብሎ እንደገጠመ ይነገራል፡፡

ሚስቴንም ውሰዳት መሬቴን እረሰው፤

በሬዬን ሽጥና ልብሲንም ግፈፈው፤

የሬሳ መውጫዬን ቤቴን አታፍርሰው፡፡

በጃዝ ካልታጀበ ካላልን በስተቀር ግጥሙ የኛም ነው፡፡ ከሚስት በስተቀር የመሬት፣ የበሬ፣ የልብስ፣ የቤት ስጋት የለብንም? በዚች አገር ውስጥ ህይወት በስጋቶች ሰርጥ መካከል የምትስለከለክ የትውልድ ጅረት አይደለችም?

**በድንጋይ ቢመታኝ መታሁት በኩበት፣**

**ምን ያደርጋል ብዬ ያለጊዜው ጉልበት፤**

እያለ የኖረ-ህዝብ ተቀጥላ አይደለንምን? ደሙን በደማችን፣ ስጋውን በስጋችን፣ ስጋቱን በስጋታችን አልወረስንም? እርግጥ ያኔ የነዳጅ መጨመር ስጋት፣ የመብራት መቆራረጥ ስጋት፣ የፕሬስ ነፃነት ስጋት፣ የስደት ስጋት... የለ ይሆናል፡፡ ደግሞም ስጋት መጨመር አያኩራራም፡፡ መቀነስ እንጂ፡፡

የጥንታዊዋ ግሪክ ፈላስፋ የሆነው ኢፒኩሪየስ (Epicurus) ..ስጋት የሌለበት የተደላደለ ህይወት መምራት የሰው ልጅ የምንጊዜም ፍላጐት ነው.. የሚል ፍልስፍናዊ አቋም ነበረው፡፡ ሰው ከስቃይ እየሸሸ ደስታን ለመያዝ የሚንደረደር የመሀል ቤት ፍጡር እንደሆነም ተናግሯል፡፡ (“Joys of the mind based on the individualistic ideal of evading suffering and attaining a quiet and joyful state of the soul.)

ኢፒኩሪየስ እንዳለው እኛ ኢትዮጵያውያን ስቃይን እየሸሸን ደስታን ለማግኘት አንንጠራራም፡፡ ከፊታችን ደስታ ስለሌለ፣ ከስቃይ በመሸሸም ስለታከትን ሁሉንም እርግፍ አድርገን ትተናል፡፡ ስቃይ የህይወት አጋራችን ሆኗል፡፡ ስጋትን ጎጆ፣ ፍርሃትንም አጥራችን አድርገናል፡፡ ይሄ ሳያንስ ገዢዎቻችን የስጋት መቃብራችን ላይ የስጋት ካባ ይደረድራሉ፡፡ የወታደሮቹ በጦር-ቃና ስልት መሰለፍ ብቻ አይደለም፡፡ ኮሽ በላለበት ቀትር የአድማ መበተኛ መኪና ውሃውን ሰድሮ ልታይ ትችላለህ፡፡ ሽራ የለበሰ ምንነቱ ያልለየ ከባድ ጦር መሳሪያ እየተጐተተ ወይንም ተጭኖ ሲያልፍ ልታይ ትችላለህ፣ የድንጋይ ውርወራን ለመከላከል የብረት ወንፊት የተገጠመለት የአድማ በታኞች ማመላለሻ መኪና ልታይ ትች ላለህ፡፡ በኢ.ቲ.ቪ. ተሳፍረው ጋደም ያልከበት ይመጡልሃል፡፡ አድማ ሲበትኑ፣ ሲገለባበጡ፣ ያልተጠመደ ቦምብ ሲያከሽፉ... እያሳዩ ያባትቱሃል፡፡ ስጋቱ ከባሰብህ ላንተና ለቤተሰቦችህ የሚበቃ ባንከር (ምሽግ) ደጅህ ላይ መቆፈር ትጀምር ይሆናል፡፡ ሆኖም የቆፈርከው ምሽግ እንደ መሬት ስር ቤት ተቆጥሮ ለኪ እንዳይመጣ ደግሞ አንድ ሌላ ስጋት ትጨምራለህ እንጂ አትቀንስም፡፡ በመጨረሻም ፍሬዴሪክ ኒቼ “Antichrist” ላይ እንዳለው በደስታ መኖር ወይም ጭራሹኑ መኖርነኳ እንደማይቻል ይገባሃል፡፡ (The impossibility of living happily or even living at all)

..ነገር በዓይን ይገባል.. በሚለው ነባር ብሒል ተማምነህ ብትጨፍንም ከስጋት አትድንም፡፡ በጆሮ የሚገባው ይላክልሃል፡፡ የኛን ታውቀዋለህና አንድ መጽሐፍ ላይ ያገኘሁትን አንድ አረፍተ ነገር ላንብብልህ፡፡ መጽሐፍ “A NEW INFORMATION ORDER OR PSYCHOLOGICAL WARFARE” ይሰኛል፡፡ ገፅ 16 ላይ እንዲህ ይላል፡፡

“Justifying its crimes and trying to make it appear respectable. To achieve this the concepts of good and evil of progress and reaction are actually transposed. For example in stories about ELSalvador the word “terrorists” stands for patriots, “fratricidal war” for the libertion struggle,“social force ” for murderers, “government” for fascists and “advisers” for American interventionists”

(ወንጀሉን አሳማኝና የተከበረ ስራ ለማስመሰል የ"ጥሩ" እና "መጥፎ" እንዲሁም የልማትና የተቃውሞ ተግባራትን አለዋውጠው ያቀርባሉ፤ ለምሳሌ ያህል ስለኤል-ሳልቫዶር የሚያትቱ ታሪኮች ውስጥ ፣አሸባሪ፣ የሚለው ቃል የሀገር ፍቅርላላቸው ይውላል፡፡ የነፃነት ትግሉን ደግሞ ቤተሰባዊ ፍጅት (ኢንተርሀሞይ) ይሉታል፡፡ ነፍሰ ገዳዮቹ "ማህበራዊ ኃይል" ተብለው ሲጠሩ "መንግስት" ደግሞ ለፋሽስቶቹ ይውላል፤ እንዲሁም የአሜሪካን ጣልቃ ገቦችን "አማካሪዎች" በሚል ይጠሩዋቸዋል፡፡)

እናስ? የኛ ይቅርና "ኤልሳልቫዶር" ብትሆን ስጋት በጆሮ አይገባም ብለህ ትከራከር ኑሯል? የምታውቀው አይምታታም? የጨበጡት አያጠራጥርም?...

እዚህ ላይ አንድ አገራዊ ብሒል እንድነግርህ ፍቀድልኝ እነሆ፡- **"ሲጠሩህ ዝምበል፣**

**ሳይጠሩህ አቤት በል፣**

**ነገሩ እንዲዘናበል፡፡"**

እናስ? "የኤልሳልቫዶር" አዝማሚያ "ነገር የማዘናበል" አይመስልህም? ኤል-ሳልቫዶርን ትተህ እስኪ ወደራስህ ተመለስ፡፡ ለመሆኑ ስጋቶችህን ቆጥረህ ታውቃለህ? ቤትህ፣ በርህ፣ ሰው መሆንህ፣ ዜግነትህ፣ ደሞዝህ፣ መማርህ፣ ብርህ፣ ሀብትህ፣ አካባቢህ፣ ገበያህ፣ ስራህ፣ ጤንነትህ፣ ነፃነትህ፣ ያለህበት ሁኔታ፣ ደህንነትህ፣ ግቢህ... በየትኛው ላይ መተማመን ይሰማሃል? እጅህ፣ እግርህ፣ አይንህ፣ አንገትህ፣ ጭንቅላትህ፣ አፍንጫህ፣ ጆሮህ፣ ህይወትህ... የትኛው ባለበት ይቆይ ይመስልሃል?